# ማጠቃለያ:- 2022 የአደጋ ጊዜ እሳት ጭስ ደንብ WAC 296-62-085

Washington State Department of Labor & Industries

## ዳራ

የሰደድ እሳት ጭስ ለዋሽንግተን ሰራተኞች እየጨመረ ያለው አደጋ ነው። ሠራተኞችን ለመጠበቅ፣ አዲስ የአደጋ ጊዜ የዱር እሳት ጭስ ደንብ ከጁን 15 እስከ ሴፕቴምበር 29 ቀን 2022 ድረስ ተግባራዊ ይሆናል።

የሰደድ እሳት ጭስ ጎጂ ኬሚካሎች እና በአየር ላይ የተንጠለጠሉ ጥቃቅን ንጥረ ነገሮችን የያዘ ነው። ይህ ጭስ ጤናማ ግለሰቦችን ሳይቀር ማንኛውንም ሰው ሊያሳምም ይችላል።

የሰደድ እሳት ጭስ መለስተኛ ምልክቶችን ሊያስከትል ይችላል:-

- ሳል።
- የሚሻክር ጉሮሮ።
- የሚያቃጥሉ አይኖች።
- ራስ ምታት።

ጭሱ የሚከተሉትን ጨምሮ ከባድ እና አንዳንድ ጊዜም ለሞት የሚዳርጉ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል።

- የደረት ሕመም እና የልብ ድካም።
- የአስም ጥቃቶች።
- የመተንፈስ ችግር።

**የጭስ መጠኖች በተደጋጋሚ ሊለወጡ ይችላሉ።** የጭስ መጠኖች አደገኛ የሚሆኑበት ጊዜ ላይ ሲደርሱ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ያ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዱር እሳት ጭስ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን ለመጠበቅ የተወሰኑ የመከላከያ እርምጃዎች መቀመጥ አለባቸው።

የአሁኑን የአየር ጥራት መረጃ ለማግኘት የሚረዱ አንዳንድ የተለመዱ የኦንላይን መሳሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- **የአየር ጥራት ካርታ** ከዋሽንግተን ስቴት የስነ-ምህዳር መምሪያ (Washington State Department of Ecology)
- **AirNow.gov** ከዩኤስ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (U.S. Environmental Protection Agency, EPA)
- **የዩኤስ የደን አገልግሎት መሳሪያዎች** (U.S. Forest Service)፣ ይህም በአየር ውስጥ ያሉ ጥቃቅን ንጥረ ነገሮችን ይለካል

**የአየር ጥራት መረጃ በዋነኝነት የሚዘገበው በሁለት መንገዶች ነው።**

- $PM_{2.5}$ ተብሎ የሚጠራው ጥቃቅን ቅንጣት።
- የአየር ጥራት መረጃ ጠቋሚ ወይም (Air Quality Index, AQI) ለ $PM_{2.5}$። AQI በመለኪያው ውስጥ $PM_{2.5}$ ን ጨምሮ አምስት ዋና ዋና የአየር ብክለትን ያስከትላል።

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የሰደድ እሳት ጭስ ጥንቃቄዎች በአሠሪዎች እና ሠራተኞች መወሰድ ያለባቸውን ደረጃዎች ያሳያል።

| **$PM_{2.5}$ በ ማይክሮግራም በኪዩቢክ ሜትር ውስጥ ($\mu g/m^3$)** | **የአየር ጥራት መረጃ ጠቋሚ ለ $PM_{2.5}$ (AQI)** |
|---|---|
| 20.5 $\mu g/m^3$ | AQI 69 |
| 35.5 $\mu g/m^3$ | AQI 101 |
| 555 $\mu g/m^3$ | ከ AQI በላይ |

**ከተቻለ ከፍተኛ የሆነ የሰደድ እሳት ጭስ በሚኖርበት ጊዜ ከቤት ውጭ ያለውን ሥራ ገድቡ።** ሠራተኞችን ከዱር እሳት ጭስ የሚከላከሉባቸው አንዳንድ መንገዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የሥራ መርሃግብሮችን መቀየር ወይም ሥራን ወደ ቤት መቀየር።
- የሥራውን አካላዊ ጥንካሬ መቀነስ ወይም የእረፍት ጊዜያትን መጨመር።
- የመተንፈሻ መሳሪያዎች መስጠት።

**የመተንፈሻ መሳሪያዎች የሠራተኞችን ሳንባዎች ለመጠበቅ አየሩን ያጣራሉ።** በትክክል የተገጠሙ የመተንፈሻ መሳሪያዎች ሠራተኛው ለሰደድ እሳት ጭስ ያለውን ተጋላጭነት በእጅጉ ሊቀንሱ ይችላሉ። ሠራተኞችን ለመጠበቅ የሚለብሰው የተለመደ መተንፈሻ መሳሪያ N95 ነው።

በአፍንጫ እና በአፍ ላይ የሚለበሱ መሃረቦች፣ ስካርፎች፣ የፊት ጭንብሎች፣ KN95'ዎች፣ ወይም ካኒተራዎች ከሰደድ እሳት ጭስ በበቂ ሁኔታ ጥበቃ አይሰጡም።

**በሰደድ እሳት ጭስ ውስጥ መሥራት ሰዎችን ሊያሳምም ይችላል።** ለሰደድ እሳት ጭስ በመጋለጥ የጤና ጉዳቶች ካጋጠሙቸው፣ ሠራተኞች ለአሠሪያቸው ማሳወቅ አለባቸው። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሠራተኞች አፋጣኝ የሕክምና እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

አሠሪዎች የአየር ጥራት አደጋን፣ አሉታዊ የጤና ችግርን ወይም ከሥራ ጋር በተያያዙ ህመም ወይም ጉዳት ምክንያት ህክምና በመፈለጉ፣ ሠራተኛው ላይ የአጸፋ እርምጃ እንዲወስዱ አይፈቀድላቸውም።

**የ2022 የሰደድ እሳት ጭስ የድንገተኛ ጊዜ ደንብ ማጠቃለያ፣** የዋሽንግተን አስተዳደር ኮድ (Washington Administrative Code, WAC) 296-62-085

በአጠቃላይ፣ የድንገተኛ ሰደድ እሳት ጭስ ደንብ ተግባራዊ የሚሆነው የጭስ መጠኖች በ 20.5 $\mu g/m^3$ (AQI 69) ወይም ከዚያ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ ነው። አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የተወሰኑ ቁጥጥሮች መኖራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ በተዘጋ ህንፃዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ውስጥ ያሉ የሥራ ቦታዎች።
- ሠራተኞች በቀን ለአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ ላነሰ የሥራ ጊዜ ይጋለጣሉ።

ለማጠቃለል፣ ደንቡ የተሸፈኑ አሠሪዎች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠይቃል፦

- የሰደድ እሳት ጭስ ምላሽ ዕቅድ እንዲኖራቸው።
- የሠራተኛውን ለጭስ የመጋለጥ ደረጃዎች ከሥራ በፊት እና ጭስ በሚኖርበት ጊዜ በእያንዳንዱ ፈረቃ ውስጥ በየጊዜው እንዲወስኑ።
- በሰደድ እሳት ጭስ አደጋዎች ላይ ሠራተኞችን እዲያሰለጥኑ።
- በሰደድ እሳት ጭስ ምክንያት ለሚመጡ የጤና ችግሮች እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ ተቆጣጣሪዎችን እዲያሰለጥኑ።
- በሰደድ እሳት ጭስ ላይ ያሉትን የመከላከያ እርምጃዎች ለሠራተኞች ያሳውቁ።

የሰደድ እሳት ጭስ ሁኔታዎች 35.5 $\mu g/m^3$ (AQI 101) በሚደርሱበት ጊዜ፣ ተጨማሪ መስፈርቶች የሚያካትቱት፦

- የጭስ መጠኖችን ለሠራተኞች ማሳወቅ።
- የመተንፈሻ መሳሪያዎችን ማቅረብ እና አጠቃቀማቸውን ማበረታታት።
- የሚቻል ሲሆን፣ ሠራተኛ ለሰደድ እሳት ጭስ ያለውን ተጋላጭነት ምገደብ።

የጭስ መጠኖች በ 555 µg/m$^3$ ወይም ከዚያ በላይ ሲሆኑ፣ ተጨማሪ የመተንፈሻ መስፈርቶች ይተገበራሉ።

አሠሪዎች ሊከተሏቸው የሚገቡትን ሙሉ መስፈርቶች **የድንገተኛ ሰደድ እሳት ጭስ ደንብ, WAC 296-62-085** ውስጥ አንብቡ።

---

*ስለ ኤጀንሲ ፕሮግራሞች እና በእርስዎ ቋንቋ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች መረጃ ለማግኘት፣ የዋሽንግተን ስቴት የሠራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች መምሪያን (Washington State Department of Labor & Industries) በ 1-800-547-8367 ያነጋግሩ። ይህ አገልግሎት ነፃ ነው።*

*በሚጠየቁበት ጊዜ፣ ለአካል ጉዳተኞች የሚሆኑ ቅርጸቶች ይገኛሉ። በ 1-800-547-8367 ላይ ደውሉ። TDD ተጠቃሚዎች፣ በ711 ይደውሉ። L&I (ሠራተኛ እና ኢንዱስትሪ) የእኩል እድል ቀጣሪ ነው።*